# ሀበሺኛ በአስር

ከሐማ ቱማ

መሰለኝ ልክ ነው ከቶም አይመስለኛል

ስንጥቅ ምላስ ወሬ አለና የለሁም ሁሉም ይመቸኛል

ማዳመጥ ልጀምር ጆሮዬን ብከፍተው

የወያኔ ቅጥፈት በድንገት መረገው ።

ዘመኑ የዋሾ ጊዜውም የገዳይ

አስመሳይ አገር ወዳድ ባገር ሁሉ ተባይ

ፈልቶ ተጠናክሮ እያፈነን ስቃይ

ዝምታው ለምን  ነው ወድቀን በ ትቢያ ላይ?

--------------------

ህጻን ልጅ ሲወለድ አምርሮ ማልቀሱ

የኑሮን ክፉነት ማን ነግሮት ነው ለእሱ?

__________

ቁልቢም ዮፍታሔ ዝቋላ ዋልድባ

ታቦት ሁሉ መናኝ ገዳምን ፍለጋ

ጳጳሱ ከጦዘ ሰው በላው ከሞተ

ሚያበቃ መስሏቸው ምለላ ስለቱ

ታደጉን ጫጫታ ወይኔና እሪታ

ስራ አጥ ልንሆን ነው ብለው ስለፈሩ

ካሉበትም ጠፍተው ምነናን መረጡ

እኛም ታዘብናቸው ኢትዮጵያን ሲረሱ

መች ሚያበቃ ሆኖ መከራው ምጸቱ?

__________

ሀገር መጥቿል አሉ አደገ ከበረ

ፈረንጅ ጡት አባትም ውሽቱን አጀበ

ድህ ሞልቶ ተርፎ መከራ እያነቀን

ያ የከፋው ትላንት ከዛሬው ተሽሎ ይበላችሁ ሲለን

መንገድ አዳሪውን ስቃይ ሰለባውን ማየት ተከልክለን ።

ብሩህ ቀን ቀጠሮ መቸም የማይመጣ

ሀገር ወዳድ ጠፍቶ ራስ መውደድ ጣጣ።

የሶፋ ፋኖነት የቅምጥ አርበኛ

ነጻነት ያልነውም አልደርስ አለ ከእኛ ።

----------

እንጣጥ እንጣጥ እያልኩ ሰማይን ልነካ

ምድርን ለቆ ዝላይ ምኞትን ጭበጣ

ከአቅም በላይ  ምኞት  የለውጥ አጋፍሪ

ቀቢጸ ተፋንም እንጦርጦስ ቀባሪ ።

-----------------------

ሁለት እሁድ ያለው ሳምንትን ፍለጋ

ሰጎንን ፍለጋ በግጨው በረሀ

ማስቀደም መከጀል ማክሰኞን ከ ሰኞ

ሙታንታ ሱሪ ላይ ዝነጣ ተብሎ

ዕንቁጣጣሽ ግንቦት ልደትም በሰኔ

ጻደቅን ያሉት ከንቱ ይዟቸው ኩነኔ ፤፡

_______________

አንተ ማነህ ብለው መልሱማ እኔ  ነኝ

እኔ ነኝ ማን ብለው መልሱ አንተ ነህ  አለኝ

እኔ አንተ አንቺ እሱ አንድ ነበር አንዴ

ባይመጣ መጋኛ የሚባል ወያኔ።

_______________

በይፋም በልብም ስንት ጊዜ አለቀስን

ስንት ጊዜ ሳቅን ጮህንም ቀስ ብለን

ደስታ አለሀዘን ሀዘን አለደስታ

ፍቅረኛ መንትዮች ማይሄዱ ለብቻ

ኮሾ ፍልስፍና ራስን ድለላ

ደስታ ካገር ጠፍቶ ሀዘን እየሞላ ።

______

ያን ግፍ ወንጀል ሽብር የዛሬው ሽፍኖት

የብዕር ቅጥረኛው የወረቀት ኩሊው ጧት ማታ ዘምቶበት

ፍቅሬ ትውስታዬ ልመስከር ጫጫታ

መጽሓፍ በርክቶ የወያኔ ኡኡታ

የወሬ ነጋሪ የሀሰት ዘመቻ

ቅጥፈት በየገጹ ቅርሻት የወያኔ

የቅጥረኛ ጩሀት አሌሆ አሌሆ ።

_______________

## ሀበሺኛ በአስር--2

ዳዊት ደጋሚውም ቁርዓን የቀራውም

ፈረንጅ ቤት ሄዶም ዶክተራ ያገኘውም

ሁሉም ተወናብዶ

ሁሉም ተደናግሮ

አዋቂ መሓይም ተማረ ያልተማረ

ሼኩ ሐጢያተኛ ቄሱ ቆብ የጣለ

ዕልም ጭልጥ አንጎል የከህደትም ቀፎ

ጀናው ሰው እያለ ባንዳ መድረክ ይዞ

ቆራቱ ሳይጠፋ ቡከኑ ተንጫጭቶ

---------

ክረምቱማ ጠፍቶ መስከረም ሲጠባ

የምን አሜከላ ፈልቶ አደይ አበባ

ፍንደቃውም በዝቶ የብሩህ ቀን ተስፋ

የገሃነምም በር ለሁሌ ሊዘጋ

ትግላችንም ቀጣይጭቆና እስኪበቃ ።

-----------

ሰይፈኛው ሚካኤል አንገትክን  ይቁረጠው

ማርያምም ትርገምህ አላህ ሞትን ይስጥህ

ለካስ ዋናው ሰይጣን ዓንተ ራስህ ነበርክ

እኛ ሰው ስንልህ !

------

ራስ ትልቅ ሆኖ ውስጡ ባዶ ቀፎ

ሀሞት ያው መራራ ወኔ ግን አጥጦ

ትልቅ ልብ ጠፋና ጨካኝ ባገር ሞልቶ

አውቅን ያሉትም ሁሉም ዜሮ ባዶ።

-----

ዝንት ዓለም ሲፈጠር

ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነው

ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር

ብሎ ያስተማረው

ወደየት ደረሰ ሃይሉ ገብረ ዮሐንስ

እሳተ ገሞራው?

በአጼው ድብደባ ስየልም ያልፈታው

በስደት ዓለምም ስቃይ የቀመሰው

ማን ዞር ብሎ አየው ማንስ ወዲያው ረሳው

የሰው መገመቻ አንዱ እኮ ይህው ነው ።

---------------

መደብ ላይ መሬት ላይ ጠፍር አልጋ

ለደላውም ፍራሽ ነበረ መተኛ

ዘመን ተቀይሮ ሰውም ተለውጦ

ህሊና ላይ እንቅልፍ ሥልጣኔ በዝቶ

በቁም መሞት ጥበብ ብልህ አሰኝቶ ።

---------------

ጉም ልጨብጥ ብዬ ስዘል ስንጠራራ

መሬት ሲቀበለኝ ሲለኝ አጉል ተስፋ

ሞኝ አጉል ሙከራ ።

ዛሬ ጠጣር ሆኖ ምኞትን ሲያጠፋ

ህልምንም ሲያደባይ ሲያስፍን ጨለማ

ደካማው ሲወድቅ ሁሉ አለቀ ብሎ

ጀግናው ግን ይገፋል ድልን ሊያገኝ ታግሎ ;

--------

ብለን ነበር እኛ ባየሩ ላይ ተኖ

ሰሚ ተመካሪካገር ሁሉ ጠፍቶ

ብዙው ተሞኘና ጠላት ማቀፍ ደርቶ

ሰይጣኑ ወያኔ ወዳጅ ነህ ተብሎ

ለፋሺስት አተላም የሚርደው በዝቶ

የእናት እንባ ጎርፍን የሚያየውም ጠፍቶ

በደም ላይ መሳለቅ ንቃት ነው ተብሎ ።

---------------

ቁረጠው በልተው ጨፍጭፈው ግደለው ማለቱ ሲያምራቸው

ከቶ ለምን ይሆን በቅድሚያ ታሪክን ማጥፋት ሚያሰኛቸው ?

ዛሬን የማይገጥሙት ሀቅ ወኔ ካላቸው ?

---------------

ፍቅር እኮ እውር ነው ያላለኝ ማን አለ

ፍቅር ያሳብዳል ያላለኝ ማን አለ

ፍቅር ለሀገር ነው ወይስ ለግለሰብ

ለዚህ ጥያቄማ መልስም ሰጪ የለ ።

---------------